# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2023
አዲስ አበባ

ማስታወሻ

እባክዎ http://www.ethiomet.gov.et ይጎብኙ

ርዕስ ገፅ


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የነበረው የአየር ....... 1

ሁኔታ ግምገማ ....... 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....... 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ....... 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....... 4

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ....... 5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 5

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....... 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....... 6

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የሚኖረው የአየር ....... 7

ሁኔታ አዝማሚያ ....... 7

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-21 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ ....... 7

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-21 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....... 7

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 8

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....... 9


# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው የቆየ ቢሆንም፤ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አንጻራዊ መጠናከር በመኖሩ ምክንያት በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ቀላል ዝናብ ተስተውሎባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የተጠናከረ ሲሆን፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቅዝቃዜው መጠን ከ 0 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነት ያህል በደብረብርሀን -1.2፣ -0.8፣ 3.2 እና 1.2፣ በሐሮማያ 1.8፣ -0.2፣ 1.6፣ 2.2፣ 2.4 እና 3.2፣ በቡኢ 3.0፣ 3.6 እና 4.6፣ አርሲ ሮቤ 1.5፣ 2.5፣ 3.5 እና 3.0፣ በቦሬ 4.8፣ ጅማ 4.0፣ 4.0፣ በጨፋ 3.6፣ 3.4 እና 3.8፣ በፍቼ 3.2 እና 4.3፣ በእምድብር 4.8 እና 4.6፣ በባሌ ሮቤ 2.4፣ 3.2 እና 4.7፣ በደብረወርቅ 4.0 እና 4.0፣ በእንዋሪ 3.8 እና 4.8፣ በአደሌ 3.0፣ 4.5፣ 4.0፣ 2.4 እና 4.0፣ በአዴት 0.3፣ 2.6፣ 2.8፣ 3.0 እና 3.4፣ በመሐል ሜዳ 4.5፣ 4.6፣ -1.5 እና 0.0 እንዲሁም በወገል ጤና 3.5፣ 1.0፣ 1.6፣ 2.4 እና 2.5 በዲግሪ ሴልሽየስ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በአዊ፣ በመካከለኛው ጎንደር፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በአሶሳ፣ በአፋር ክልል ዞን 03 ና 05 በጥቂት ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በድሬዳዋ፣ በአርሲ፣ በባሌና ምስራቅ ባሌ ሰሜናዊው ክፍል፣ የምዕራብ ኦሞ እንዲሁም በነገሌና በያቤሎ ከ5-35 ሚሜ የሚደርስ ከ1-2 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በመጀመሪዎቹ ሁለት ቀናት በተመዘገበው አነስተኛ የዝናብ መጠን ምክንያት በአዊና በመካከለኛው ጎንደር፣ በአብዛኛው የቤንሻጉል ጉምዝ ክልሎች፣ ከአፋር ክልል በዞን 03 ና 05 በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በድሬዳዋ፣ በአርሲና በጥቂት ባሌና ምስራቅ ባሌ ሰሜናዊው ክፍል፣ እንዲሁም በያቤሎና በነገሌ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች | መደበኛ | ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት አመቺ ነበረ፡፡ ከደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የነበረው የማለዳና የሌሊቱ ቅዝቃዜ በአንጻራዊ ሁኔታ በመጨመሩ በአንዳንድ ቅዝቃዜን መቋቋም በማይችሉ አትክልቶች ፍራፍሬዎች በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ ሰብሎች እድገት ላይም ሆነ በአንዳንድ የቤት እንስሳት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል የሚችል ጠንከር ያለ የቅዝቃዜ ሁኔታ ተስተውሏል። በሌላ በኩል በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው እርጥበት ከመኖሩ ጋር ተያይዞ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ጎን የነበረዉ ሲሆን፤ በተለይም የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ነበርው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈናቸው የጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው የቆየ ቢሆንም፤ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት በጥቂት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ማለትም በመካከለኛው አዋሽ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ሆኖም ባሳለፍናቸው አስር ቀናት የነበረው እርጥበት በግድቦች የውሃ መጠን ላይ የጎላ ተጽዕኖ እንዳልነበረው ከግድቦች የውሃ መጠን መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች በአብዛኛው ቦታዎቻቸው ላይ የበጋው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በቀጣዮቹ አስር ቀናት በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ አመዝኖ ይቆያል:: ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምሥራቅ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በጥቂት ሥፍራዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ።


በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት አሥር ቀናትም ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ምክንያት በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራብ እንዲሁም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን የሚኖራቸው ሲሆንና ከዚሁ ጋር በተያያዘም አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

<u>በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፤ የአፋር ዞን 2 እና 4፤ የመካከለኛውና ምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ እና ሆሮጉድሩ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የቤንች ማጂ ዞን እንዲሁም ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሸካ እና ከፋ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡</u>




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-21 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-21 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጃንዋሪ ወር ሁለተኛው አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚከናውኑበት ወቅት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች መጠነኛ እርጥበት ሊያገኙ የሚችሉበት ወቅት ነው።

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ወር ሁለተኛው አስር ቀናት የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ በቀጣይነት እንደሚስተዋል ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ ቀደም ብለው የተሰበሰቡ ሰብሎችን ለመውቃትና በተዘጋጀላቸው ስፍራ ለማከማቸትም ሆነ ወደገበያ ለማውጣት የሚያስችል በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በድህረ ሰብል ስብሰባ ስራዎች የምርት ብክነት እንዳይኖር አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ እንዲያከናውኑ ይመከራሉ። በሌላ መልኩ ከሚጠበቀው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ቅዝቃዜ የመቋቋም አቅማቸው ዝቅተኛ በሆኑና በመስኖ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎች፣ በጓሮ አትክልቶችና በቋሚ ተክሎች እድገት ላይም ሆነ በአንዳንድ የቤት እንስሳት ላይ የተወሰነ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል። ስለሆነም በዘርፉ የተሰማሩ አርሶ አደሮችና የሚመለከታቸው አካላት የአካባቢን ሙቀት ሊጨምሩ የሚችሉ ዘዴዎችን በመጠቀም በቅዝቃዜ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ይመከራል። በሌላ መልኩ በሰሜን ምሥራቅ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው የእርጥበት መሻሻል ሊኖር እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲሻሻልና የበልግ ወቅት እርሻን አስቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወን አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው በመረዳት አስፈላጊውን ዝግጅት ከወዲሁ እንዲያደርጉ ይመከራል።

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጃንዋሪ ወር ሁለተኛዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰስ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ የሚስተዋልበት ጊዜ ነው። ሆኖም ግን ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙበት ወቅት ነው።

በተሰጠው የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በመጪዎቹ የጃንዋሪ ሁለተኛው አስር ቀናት በተወሰኑ ተፋሰሶች ላይ ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ለመጥቀስም ያህል የላይኛው እና የመካከለኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እና በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ናቸው፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ግን በደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ስር እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡